# የልመና እርጥባንና መዘዙ

*በላይነህ አባተ ( abatebelai@yahoo.com)* *ሰኔ ሁለት ሺህ አንድ ዓ.ም.*

ሰው በተፈጥሮው ማህበራዊ እንስሳ ነው። በማህበራዊ ባህሪውም ቤተሰብ፣ ጉርብትና፣ ቀበሌ፣ ወረዳ፣ አውራጃ፣ ክፍለ-ሀገርና አገርም መስርቶ አብሮ ይኖራል። ዛሬ ዛሬ እንዲያውም አገሮችም እየተቀላቀሉ መጥተዋል። የአውሮጳንና የሰሜን አሜሪካን አገሮችን ትስስር ልብ ይሏል። እንደ አለመታደል ሆኖ የተዘረጉትን የሰውን ልጅ ተፈጥሯዊ ህጎች ብቻ ሳይሆን በአውሬዎቸም ጭምር ያለውን ደመነፍሳዊ ሥረዓት እንደ ገመድ ቦጫጭቀን ለማህበራዊ ኑሮ ክልል በመፍጠር ላይ ያለን እኛ ብቻ ነን። ሰው በማህበራዊ እንስሳነቱ አብሮ መኖር ብቻ ሳይሆን በመከራም ሆነ በደስታ ጊዜ ይረዳዳል። አፍሪካዊ ጎበዝ ጎጆውን ሲሰራ ሌሎች ጎበዛዝት ተሰብስበው ግድግዳውን በማቆምና ጣራውን በመጫኑ ስራ ላይ ይረዱታል። ሰርግ ሲሰረግም ዘመድ አዝማድና የሰፈር ሕዝብ ሰብሰብ ብሎ አብሮ ይጨፍራል። ሐዘን ሲመጣም እድርተኛ አብሮ እንባ ያነባል፣ አስከሬን ይሸከማል፣ መቃብር ቆፍሮ ይቀብራል። ምእራባውያን እንደዚሁ አውሎ ነፋስ፣ ጎርፍና ማእበል ሲያጠቃቸው ለተጎዱት ወገኖቻቸው ገንዘብ በማዋጣት፣ ልብስ በመለገስ፣ መጠለያ በማዘጋጀት ወዘተ ይረዳዳሉ። "ዱባና ቅል ለየቅል" እንደሚባለው እርዳታ ማድረግና **እርጥባን** መርጠብ ግን የተለያዩ ነገሮች ናቸው።

***ለመሆኑ እርጥባን ምንድን ነው?*** በጠቢያውያን ባህል መሰረት እርጥባን ሰው ከፍተኛ የሆነ ያልታሰበ የንብረት ወይም የሐብት ጥፋት ሲደርስበት የአካባቢው ሕዝብ ርህራሄ ተሰምቶት የሚለግሰው እርዳታ ማለት ነው። እርጥባን የሚገኘው በልመና ሳይሆን በስጦታ መልክ ነው። እርጥባን ዘለቄታዊ ሳይሆን ጊዜአዊ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው ከብቶቹ በወረርሽኝ በሽታ አልቀው የሚያርስበት በሬ፣ የሚያልበው ጥገት ወዘተርፌ አጥቶ በድንገት መከራ ውስጥ ሲገባ ሰው በሐዘኔታ የሚችለውን ያህል እርጥባን ይረጥበዋል። እርጥባኑም በእህል፣ በገንዘብ ወይም በሌላ መልክ ሊሆን ይችላል። እርጥባን የመከራ ምልክት ነው። እርጥባን ሐዘንን ተከትሎ የሚመጣ ነገር ነው። እርጥባን የሚቀበል ሰው መንፈሱ የተሰበረ፤ስጋውም የደቀቀ ነው። እርጥባን ከሞት ለማምለጥ ወይም ከምንረግጠው መሬት ውስጥ ላለመዋል ሲሉ የሚቀበሉት ርዳታ ነው። እርጥባን አንገትን ሰብሮ የሚቀበሉት የነፍስ ማትረፊያ ምጽዋእት ነው። አዎ እርጥባን ህይወትን አትርፎ ከሞቱት በላይ የሚያውል ነገር ግን ከቆሙት እጅግ ዝቅ አድርጎ የሚያስቅምጥ ጉዳይ ነው። በተለይ መከራ ያልደረሰበት ሰው እርጥባን ከበላ በቁሙ የውርደት ሞት እንደሞተ ይቆጠራል። እርጥባን የሚጠይቁት የአፍሪካ ገዥዎች ከዚህ በቁማቸው የውርደት ሞት ከሚሞቱት እርጥባን ጠያቂቆች የሚመመደቡ ናቸው። ደሳሳ ጎጆውን አቃጥሎ ወይም ኮስማና በሬዎቹን ሆነ ብሎ አጥፍቶ ርጥባን እንደሚጠብቅ አጭበርባሪ፤ የአፍሪካ ገዥዎችም የሕዝብን አምስት ሕዋሳቶች ከአእምሮ አለያይተውና እግረ ተወርች አስረው ለርሃብ፣ ለበሽታና ሞት ይዳርጉና ልጅ አዋቂው እንደ ቅጠል ሲረግፍ ወደ ምእራብ አንጋጠው የ"እርጥባን ያለህ" ይላሉ። ከላይ በተገለጸው መንገድ በአግባቡ ሳይሆን በእንዲህ አይነት ልመና የሚገኘውን እርጥባን **የልመና እርጥባን** እለዋለሁ።

***እርጥባን በሰው አካልና መንፈስ ላይ የሚኖረው ተጽእኖ*** - ሊቃውንት ስለ ሰው አካልና መንፈስ ከጥንት ጀምሮ ብዙ ብለዋል። ከዚህ በፊት በሌላ ጽሑፍ ለመግለጽ እንደሞከርኩት[1] ኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ፈላስፋዎች ስለሰው ልጅ አካልና መንፈስ ራሱን የቻለ ትንታኔ አላቸው። በዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ላይ እንደተፃፈው [2] ሰውን ባምሳሉ እግዚአብሔር ፈጠረው ብለው ያምናሉ። በመቀጠልም ሰው የተሰራው ከአፈር፣ ከውኃ፣ ከሳትና ከነፋስ ነው ይላሉ። [3,4] (መረጃውን ከታች ይመልከቱ) ይህ ከግሪኩ ፈላስፋ ኢምፔንዱክልስ[5[ አስተሳሰብ ጋር ይመሳሰላል። ያወቀላቸው ብዙም የለም እንጅ ኢትዮጵያውያን ፈላስፎች የሰውን ትርጓሜ ስጋና መንፈስ ላይ ብቻ ላይ አላቆሙትም። አፈሩ፣ ዉሃውና ሙቀቱ በስጋ ዉስጥ ያሉ ናቸው። ይህ ሌሎቹ ፈላስፍች ስጋ (matter) ከሚሉት ጋር ይመሳሰላል። ከሌሎች ፈላስፎች በተለዩ መንገድ ነፋስን ጥሩ አድርገው በዚህ መልክ ይተነትኑታል። ነፋስ ሶስት ባህሪዎች አሏት ይላሉ። እነዚህም **ነባቢት፣ ልባዊትና ህዋዊት** ይባላሉ። እነዚህ ሶስቱ በአንድነት ወይም ነፋስ በጥቅሉ ሌሎች ፈላስፎች መንፈስ (mind) ከሚሉት ጋር ይመሳሰላል ማለት ነው። ነባቢት የሚሏት የምትናገረዋን የህይወት ክፍል ነው። ልባዊት ብለው የሚጠሯት የምታስበዋን ወይም የምታስተዉለዋን የሕይወት ክፍል ሲሆን ህያዊት የሚሏት ደግሞ የማትሞተዋን፤ እንደስራዋ መንግስተ-ሰማይት ወይም ሲኦል ትገባለች የምትባለዋን የህይወት ክፍል ነው።




ዘመናዊው የሥነ-ህይወት ጥናት (biology) እንደዚሁ ሰውን የፈጠረው ማነው የሚለውን በተገቢው መንገድ መመለስ ቢያቅተውም ሰው ከስጋና ከህሊና (conscience) የተገነባ መሆኑን በተለያየ መልክ ይጠቁማል። ስጋም ከስድሳ እስከ ሰባ ከመቶ ዉኃ ነው። የተቀረውም ከፕሮቲን፣ ካርቦሃይድሬት፣ ፋት፣ ሚኒራልና ቫይታሚን የተገነባ ነው። የምግብ አይነቶችም የሚከፈሉት በዚሁ የሰው ስጋ በተሰራበት ንጥረ ነገሮች መልክ ነው። በስጋውና በዉኃው ዉስጥም የበላነው ምግብ ኦክስጅን በሚባል አየር ወይም ካለኦክስጅን ሲቃጠል የሚመነጭ ሙቀት አለ ይለናል። [6,7] እንግዲህ ውኃ ያው ውኃ ነው። ከላይ የተጠቀሱት ንጥረ-ነገሮች አፈርን ይተካሉ፤ ሙቀቱም እሳትን ይወክላል። ህሊና የሰፈነበትን አእምሮንም ያየን እንደሁ የስሜት ህዋሳት ያሰባሰቡትን የሚያወጣ የሚያወርድ የአእምሮ ክፍል አለ። ይኸንን የልባዊት ቦታ ማለት ይቻላል። በመናገር ወይም በመጻፍ ሐሳብን እንድንገልጽ የሚያስችል የአንጎል ክፍል እንደዚሁ አለ። ይኸንንም የነባቢት ስፍራ ብሎ መሰየም ይቻላል። ስለዚህ የኢትዮጵያውን ተፈላሳፊዎች የተውልን የምርምር ውጤት ለዘመኑ ሳይንስ እጅግ የሚቀርብ ይመስለኛል።

በተለምዶ ሰማይ ቤት በምንለው ስፍራ የሚኖራቸው ቦታ በውል ባናውቅም በምድር ላይ ግን ከላይ የተገለጹት ስጋና መንፈስ(ህሊና) አብረው ይኖራሉ። በአይኑ አይቶ፣ በእጁ ዳሶ፤ በአፍንጫው አሽትቶ ወይም በምላሱ ቀምሶ ነባራዊነቱን ያረገገጠ ባይኖርም መንፈስ ወይም ህሊና በአካል ውስጥ በተይለም በራስ ቅል ውስጥ እንዳለ ይገመታል። “ለሐጥዓን የወረደ ለጻድቃን ይተርፋል!” እንደሚባለው ሁሉ ስጋን የወቀጠ ነገር ሁሉ ህሊናን ወይም መንፈስንም የመነሽም እድል እንዳለው መገመት አያዳግትም። ለምሳሌ ስጋን የጨቀጨቀ እርጥባን መንፈስንም ጥሩ አድርጎ ይወጋል። ስጋን ያጠቃ እርጥባን ምን ያህል የራስን መንፈስን እንደሚጎዳ በድሃ አገሮች እርጥባንን ተከትሎ የሚከሰተውን የአገር ክህደት፣ ቅጽበታዊ የባህልና የሃይማኖት ለውጥ ማየቱ ይበቃል።

**የልመና እርጥባን በምን መንገድ መንፈስን ያኮስሳል?** ይህን ጥያቄ በሚገባ ለመምለስ አያሌ ሁለገብ ጥናቶች ማከናወንን ያስፈልጋል። አንዳንድ የስነ-ልቡናና የአእምሮ ጥናቶች ሰርተው የማያገኙት ነገር አንጎልን(ስጋን) እንደማያነቃቃ ይናገራሉ።[8] ዳሩ ግን የልመና እርጥባን እንዴት መንፈስን እንደሚሰልብ በውል የታወቀ ሳይንሳዊ ወይም ሥነ-ልቡናዊ መንገድ (mechanism) ያለ አይመስለኝም። መላምት መሰንዘር ካስፈለገ ግን ***ሐይል ወይም ጉልበት (ወዝ=ላብ) አይፈጠርም ወይም አይጠፋም (Energy cannot be created or destroyed)*** የሚለው ህግ የሚገልጸው ይመስለኛል። ከክርስቶስ ልደት 500ና 600 አመት በፊት ከቴልስ ጀመሮ ሀይል=ጉልበት (*Energy*) ወይም ላብ ከአንዱ ወደ ሌላው የሚተላለፍ እንጅ የማይጠፋ መሆኑ በምርምር ሲረጋገጥ ቆይቷል። ቴልስ ደግሞ በውሃ አማካኝነት እንደሚተላለፍ ተናግሯል።[5] ጋሊሊዮ በበኩሉ በፔንዱለም ውስጥ ያለ የሐይል ክምችት (potential energy) ፔንዱለሙ ሲንቀሳቀስ ወደ ተንቀሳቃሽ ሐይል (kinetic energy) እንደሚቀየር ነገር ግን እንደማይጠፋ በሙከራ አሳይቷል። በኋላም አልበርት አንስታይን ለበጎ ነገር በሰራው ዳሩ ግን ተንኮለኛው ሰው ቦንብ በሚሰራበት ቀመሩ $E = mc^2$ አንዱ አይነት ላብ ከአንዱ ወደ ሌላው አይነት እንደሚቀየር እንጅ እንደማይጠፋ አረጋግጧል።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው የልመና እርጥባን ሳይለፉ ሳይግሩ የሚያገኙት ንብረት ነው። ያ ንብረት ግን የሰው ላብ ሳይፈስበት የተመረተ ወይም የተፈጠረ ነገር ሳይሆን የሌላ ሰው ጉልበት የፈሰሰበት ነው። እንግዲህ እርጥባን የሆነ ነገር ሁሉ በውስጡ የሌላ ሰው(ሕዝብ) ወዝ አለበት። ይህ ወዝ ወይም ላብ (*Energy*) የሚመነጨው ደግሞ ከሌላ ሰው ስጋ ነው። ያ የሌላ ሰው ስጋ ደግሞ የሌላ ሰው ነፍስ (ህይወት) ወይም መንፈስ ከፍና የያዘ ነው። ስለዚህ የእርጥባንን ምግብ (ውሃ፣ ፕሮቲን፣ ካርቦሃይድሬት፣ ስብ፣ ቫይታሚንና ሚኒራል) ስንበላ ወይም የእርጥባን ልብስ ስንለብስ በገላችን ስጋ ላይ እያስቅመጥን ያለነው የሌላውን ሰው አካል ላብ (ሀይል= ጉልበት=ወዝ) ነው ማለት ነው። አልበርት አነስታይን ወይም ሌሎቹ

እንዳሉት ሐይል (ጉልበት) እንደዚሁም ቁስ-አካል(matter) ስለማይጠፉ የምንንቀሳቀሰው በረጠበን ሰው ጉልበት፣ የለበስነውም የረጠበንንን ሰው ስጋ ነው ማለት ነው። ይህ ማለት ተሸክመነው የምንዞረው ገላም የረጠበን ሰው ገላ ነው ማለት ነው። ይህ የሌላ ሰው ገላ ደግሞ ውሎ ሲያድር የራስን መንፈስ ማኮስመኑና ማድቀቁ አይቀርም። ድሮውንስ የሌላ ሰው ገላ ከራስ መንፈስ ጋር እንዴት ተስማምቶ መኖር ይቻለዋል? ውሻ በበላበት የሚጮኸው ወዶ አይምስለኝም። ጌታው ወዙን በጉርሻ መልክ ስለሰጠውና የጌታውን ስጋ(ወዝ) በተዘዋዋሪ መንገድ ስለለበሰ ወሮታ ለመክፈልና ታማኝነቱን ለጌታው ለማስመስከርም ይመስለኛል። በተመሳሳይ መንገድ እርዳታ ወይም እርጥባን የሚቀበሉ አገሮችን ገዥዎችን ሁሉ ለአንድ አፍታ ፈትሹ። ይነስም ይብዛም እርጥባኑን የሰጧቸው ሰዎች( ወይም ሕዝቦች) ፍላጎት ለማሟላት ደፋ ቀና ሲሉ ውለው ያድራሉ። ይኸንንም የሚያደርጉት ወደው አይመስለኝም። ከላይ የጠቀስነው ጉልበት ወይም ሐይል በእርጥባን መልክ በጨጓራቸው ተፈጭቶ በደማቸው ተሰራጭቶ ስጋቸውን አሳብጦ(የውሸት እብጠት) መንፈሳቸውን ግን ስላቀለጠው ይመስለኛል።

**የልመና እርጥባን በአፍሪካ** - እንክት ባለ በርሃ ላይ ተሰጥተው የሚውሉ እንደ እስራኤል ያሉ አገሮች ከበለጸጉት አገሮች መሪዎች ጋር እኩል ሊነጋገሩ በሚችሉ መሪዎች ሲመሩ፤ አብዛኞች የአፍሪካ አገሮች ግን የልመና አኩፋዳ ተሸክመው እርጥባን ለምነው በሌላ አነጋገር የሌላ ሰው ስጋ ተሸክመው ወይም በሌላ ሰው ሐይል በሚንቀሳቀሱ ከንቱዎች ይገዛሉ። እነዚህ ከንቱ ገዥዎችም ከላይ እንደተገለጽው የመጀመሪያው ለማዳ እንስሳ ሁሉ አብዛኛውን ጊዜአቸውን የሚያጠፉት የረጠቧቸውን ሐይሎች ግንባር ሲያዩ፣ እግራቸውን ሲያሹና ሸተት ወረድ ብለው ሲታዘዙ ነው። በኢትዮጵያ 90% የሚሆነውን የአገሪቱ በጀት የልመና እርጥባን ነው ተባለና አረፈው። ከዚህ የከፋ የአገር ዜና ደግሞ ይሰማ ይሆን?

ተሻግሮ ሁለት አገር አሞናሙኖ ቀልቦ የሚያድረው የአባይና የሌሎችም ወንዞች እናት የሆነቸው ጦቢያ ሙሉ በሙሉ በልመና እርጥባን የመተዳደሯን ሁኔታ ሳስበው ይዘገንነኛል። ነገ ከነገ ወዲያ የማናያቸው የልጅ ልጆቻችን (እኛ ከመቃብር ውስጥ ሆነን ማለት ነው) "ጦቢያ ባህር አልባ የሆነችው፣ ባእድ በቀጠቀጠው የቋንቋ ቢላዋ የተሰነጣጠቀችው፣ ሙሉ በሙሉ በልመና እርጥባን ትተዳደር የነበረው በአያቶቻችን ዘመን ነበር!" እያሉ ሊያፍሩብንና አንገታቸውን ሲደፉብን ይታየኛል። በአራቱም አቅጣጫ ተጎንትላ የድሮ ውበቷን ያጣች፣ ፊቷን ነጭታ ጠባሳ በጠባስ የሆነች፣ በችጋርና በበሽታ ደቃ መጣፉ እንዳለው እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ሳይሆን ወደ ረጣቢዎች የዘረጋች አገር የምትረከቡ ልጆችና የልጅ-ልጆች ሆይ! በኛ ዘመን ለተፈጸመው ክህደትና ኪሳራ ራሴን ከተጠያቂነት የማወጣበት ብዙም አሳማኝ ምክንያት የለኝም። ነገር ግን ይህንን የምታዝኑትን ሐዘን በወቅቱ አንገቴን ደፍቼ እንዳዘንኩበት፤ የምታፍሩበትን ሐፍረትም በጊዜው እሳት አጠገብ እንደተቀመጠ ላስቲክ እስከምኮማተር ድረስ እንደተሸማቀኩበት ተረዱልኝ።

**ሳይለምኑ ለማኝ፤ ሳይረጠቡ ተረጣቢ መባል-** የሚያሳዝነው ነገር ሳይፈለጉ እንጣጥ ብለው ትከሻ ላይ የተጎመሩ ጉማሬዎች (ፕሮፌሰር አይቴ እንደሚጠሯቸው) በሚያደርጉት የማያቋርጥ የእርጥባን ልመና ምክንያት የአፍሪካ ሕዝብ ሳይለምንና እርጥባን ሳይጠይቅ እንደለማኝና ተረጣቢ መቆጠሩ ነው። ጉማሬዎቹ የልመና ከረጢት ይዘው የሚዞሩት "ሕዝባችን በችጋርና በበሽታ አለቀ" እያሉ ነው። ችጋርና በሽታውን በአፍሪካ ምድር እነሱ እንዳልዘሩት ሁሉ ማለት ነው። ታዲያ በራበው፣ በታመመውም ሆነ በሞተው ስም ለምነው የሚረጠቡት እርጥባን የሚደልበውና ተውጦ የሚያልቀው እዚያው ከተረጣቢዎቹ ሰፈርና የእርጥባን ፍርፋሪ ለመለቃቀም ሲሉ ተቀጥረው ከሚያገለግሉት የርጥባን-ለማኝ አገልጋዮች አካባቢ ነው። ይህ ማለት የአፍሪካ እርጥባን-ለማኞችና የእነርሱም አሽከሮች አካል የተገነባው በእርጥባን ገንዘብ በተገዛ ምግብ ነው ማለት ነው። ስለዚህ ለአፍሪካ ሕዝብ ከዚህ የልመና እርጥባን የሚተርፈው እርጥባን በልቶ በፈረጠመ ክንድ ፍዳውን ማየት፤ ባላሸተተውና ባልቀመሰው እርጥባን ሰበብ እርጥባን-ተቀባይ እየተባለ በታሪክ መመዝገብና በሚረጥቡት ዘንድም መመጻደቂያ መሆን ነው።

ባጠቃላይ ዶ/ር ዳንቢሳ ሞዮ "በድን-እርዳታ" (ትርጉም የራሴ)[9] በሚለው መጽሐፋቸው እንደገለጹት የልመና እርጥባን ለእድገት እንቅፋት ከመሆኑም በተጨማሪ የረጣቢን ስጋ አልብሶ መንፈስን ያኮስሳል፣ ማንነትም (identity) ያጠፋል። ከዚህም ባሻገር የልመና እርጥባን ጠባሳ በዘር እንደሚተላለፍ በሽታ ከትውልድ ትውልድ በታሪክ መርከብነት እየተሸጋገረ አንገትን ያስደፋል፤ መንፈስንም ይሰልባል። ይህንን አደገኛ የመንፈስ በሽታ ለመቆጣጠር እንዲቻል አፍሪካ ከሚረጥቡ ባለንብረቶችና ከሚረጠቡ ለማኝ-ገዥዎች መገላገል ያሸዋል። አመሰግናለሁ።


***ዋቢ***

*1.ለመሆኑ ሰው ምንድነው? www.addisvoice.com/article/sew2.pdf 2..መጽሐፍ ቅዱስ፤ ኦሪት ዘፍጥረት 1፡26-28*
*3.መላእከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ፤ መድሎተ አሚን 4.መላእከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ፤ ሆኩሁ-ሃይማኖት.*
*5.Frost, Jr; Man's place in the universe; great philosophers-6$^{th}$ edition 6.Guyton: Text book of Medical Physiology*
*7.Grey's Anatomy: 39$^{th}$ Edition Gelilo's Pendulum expt*
*8. Zink, C et al; Human Striatal Response to Salient Nonrewarding Stimuli, Journal of Neurost,2003, 23(22): 8092-8097*
*9.Dambisa Moyo; Dead AID; Why AID is not working and how there is a better way for Africa, First Edition, 2009*